# መመሪያ

**ኤፌ፡4፡2-3**

በትህትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሱ **በሰላም** ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፡፡

1. **የአንድን ሰው ችግር ለማቃለል አለመሞከር**
   እኛ እዚህ ያለነው የሌሎችን ችግር ለማቃለል አይደለም፡፡ ለሰው ችግር መፍተሄ የሚያመጣው ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ እኛ እዚህ ያለነው የወገኖቻችንን የውስጥ ስሜት ማዳመጥ፣እነሱን መውደድና ከእነርሱ ጋር ሕብረትን ለመፍጠር ነው፡፡
2. **ሚስጥርን መጠበቅና አባላት እርስ በራሳቸው የሚተማመኑበትን አካባቢ መፍጠር**
   በቡድኑ የተወራው ነገር ወደ ውጭ መውጣት የለበትም፡፡
   ይህ እያንዳንዱ ሰው የውስጡን ሀሳብ በነፃነት የሚገልጽበትና መተማመን የሚፈጠርበት ቦታ ነው፡፡
3. **ሌሎች እንዲናገሩ ዕድል መስጠት**
   ጊዜህን በአግባቡ በመጠቀም ሌሎችም የውስጣቸውን ሀሳብ እንዲያካፍሉ ዕድል ስጥ፡፡
4. **አንድ ሰው እየተናገረ ባለበት ሰዓት በቡድኑ ውስጥ ከጎን ካለው ሰው ጋር ማውራት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡**
   እንዲያወራ ሳይፈቀድለት ከሌላ ሰው ጋር የሚያወራ ሰው ቡድኑን ይረብሻል፡፡
5. **ከርዕሱ ሀሳብ አለውጣት**
   በቡድኑ ዋና ሀሳብ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን የቡድኑ አባል በራሱ ላይ ወይም ከቤተሰቡ ውስጥ ችግር ስለደረሰበት ሰው ለመናገር ቢፈልግ አትከልክለው፡፡ በመሃል ስለዚህ ነገር ከተነጋገርክ በኋላ ወደ ዋናው ርዕስ ተመለስ፡፡

**ማቴ፡18፡**

ለግጭት መፍተሄ ለማምጣት እንትጋለን፡፡ **ሰ ላ ም!**